ሴፕቴምበር 2016 QuickNotes ቁ. 2

**ምዝገባ ለአዲስ የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፕ ክፍት ነው**

MCPS Parent Academy (የወላጅ አካዴሚ) ለወላጆችና ለማህበረሰቡ አባላት የልጆቻቸውን የትም/ቤት ስኬት ለመደገፍ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ጥቆማዎች የሚያቀርቡ ነፃ አውደ ጥናቶች እንዲከታተሉ እድል ይሰጣል። የፎል ወራት ዎርክሾፖች አያምልጧችሁ፣ በተለያዩ ርእሶች የሚሰጡ፣ ትክክለኛውን ኮሌጅ መምረጥ፣ ወጣቶች ጭንቀትን እንዲያስተዳድሩ ማገዝ፣ የኮምፒውተር ደህንነት/cybersafety እና ማህበራዊ ሚድያ፣ ልዩ ትምህርት፣ እና የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነትን ለይቶ ማወቅና ማስታወቅን ጨምሮ።

የወላጅ አካዴሚ ዎርክሾፖች ነፃ ናቸው። የልጆች እንክብካቤና የትርጉም አገልግሎቶች በሁሉም ስብሰባዎች ይቀርባሉ። የኮርሶች የተሟላ ዝርዝር በየወላጅ አካዴሚ ድርጣብያ ይገኛል።

**ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለቤተሰቦች የነፃ ፋይናንሳዊ እርዳታ ዎርክሾፕ ሊሰጡ ነው**

ስለ ኮሌጅ እና እንዴት እንደሚከፈልበት ማገናዘብ ጀምራችሁ ከሆነ፣ በፎል ወራት በሙሉ በMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚካሄደው በነፃ የፋይናንስ እርዳታ ዎርክሾፖች ተገኝታችሁ ተማሩ። ፋይናንሳዊ እርዳታ ምን እንደሆነ፣ ምን አይነት የፋይናንሳዊ እርዳታዎች እንዳሉ እና ተማሪዎች በዕርዳታ ፈላጊነት ላይ የተመሠረተ ፋይናንሳዊ እርዳታ (need-based financial aid) ማመልከት እንዴት እንደሚችሉ ወላጆችና ተማሪዎች በነዚህ አውደ ጥናቶች ይማራሉ። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ት/ቤት ጋር ይገናኙ።

**ኦክቶበር 5 ወደ ት/ቤት በእግር መጓዝ!**
ቀኑን በጤናማ መንገድ መጀመር ትፈልጋላችሁ ወይ? ልጃችሁን ወደ ት/ቤት በእግር በመውሰድ ቀስቅሱት! የInternational Walk to School Day/አለም-አቀፍ የእግር ጉዞ ወደ ት/ቤት ቀን በአል ሮብ፣ ኦክቶ. 5 ለማክበር በመቶዎች የሚቆጠሩ የMontgomery County ተማሪዎች እና ወላጆችን ተቀላቀሉ። አለም-አቀፍ የእግር ጉዞ ወደ ት/ቤት ቀን የተመሰረተው በ1997 ሲሆን የማህበረሰብ መሪዎችና ልጆችን ለማገናኘትና ማህበረሰቦችን ይበልጥ በእግር ተጓዦች እንዲሆኑ ለማነቃቃት ነው። በአገር ውስጥ በሽዎች በሚቆጠሩ ት/ቤቶች እና በአለም አቀፍ ደሞ ከ40 በላይ በሆኑ አገሮች ይከበራል።

በእግር ወደ ት/ቤት መሄድ ጤናን ለማጠናከር፣ ለእግር ጉዞ ሰላማዊ መንገዶችን ለመለየት፣ እና የአየርን ጤና ለማሻሻል ታላቅ ዘዴ ነው። አለም-አቀፍ የእግር ጉዞ ወደ ት/ቤት ቀን ልጃችሁን ሰላማዊ/ጤናማ የአረማመድ ክሂሎቶች እንዲማርና እንዲለማመድ ለማገዝ ለናንተ ታላቅ እድል ነው። በእግር ለመጓዝ ከልጃችሁ ት/ቤት ከመጠን በላይ ርቃችሁ የምትኖሩ ከሆነ፣ ርቀቱን በከፊል በመኪና ተጓዙ፣ ከዚያም መኪናችሁን በአግባቡ አቁማችሁ የቀረውን በእግራችሁ ተጓዙ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የMontgomery CountySafe Routes to School ድርጣብያ ጎብኙ።

**ስለ ኮንሶርሺያ እና ልዩ የማመልከቻ ፕሮግራሞች ይበልጥ ይማሩ**
የNortheast (NEC) እና የDowncounty (DCC) ኮንሶርሻዎች እና የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት የማመልከቻ ፕሮግራሞች የመረጃ ስብሰባዎች በሰፕተምበር እና በኦክቶበር ይካሄዳሉ። NEC ወይም DCC የሚኖሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አማራጮች፣ ኮንሶርሺያ ት/ቤቶች፡ የChoice ሂደትና ልዩ የማመልከቻ ፕሮግራሞች መረጃዎች ያገኛሉ። ማመልከቻዎች በት/ቤቶች ወይም በMCPS ድርጣብያ ሴፕቴምበር መጨረሻ ላይ ይገኛሉ።

ስለ ኤሌሜንታሪ የከፍተኛ ተስጥኦ ማእከሎች ለመማር ለሚፈልጉ የ3ኛ ክፍል ተማሪ ቤተሰቦች በኦክቶበር ወር የመረጃ ስብሰባዎች ተዘጋጅተዋል። ማመልከቻዎች ወደየቤታችሁ በሰፕቴምበር ወር በፖስታ ይላካሉ፣ በድረ ገፁም እንዲገኙ ይደረጋል።

ስለ መካከለኛ ት/ቤት ማግኔት ኮንሶርሺየምና የመካከለኛ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራሞች ለመማር ፍላጎት ላላቸው የ5ኛ ክፍል ተማሪዎችና ወላጆቻቸው የሚሆኑ የመግለጫ ስብሰባዎች በሰፕቴምበርና በኦክቶበር በፕሮግራም ተይዘዋል። ማመልከቻዎች በሰፕቴምበር መጨረሻ ላይ በት/ቤቶችና በMCPSድረገፅ}ይገኛሉ።

**በMontgomery County አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ይሳተፉ!**
በካውንቲ-አቀፍ ደረጃ ለሚከበረው፣ ለኦክግቶ. 16-23 ለተመደበው፣ የMontgomery County አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ተዘጋጁ። የተለያዩ የአካባቢ ትርፍ-የለሽ ድርጅቶችን፣ ት/ቤቶች፣ እና የመንግስት ወኪል ድርጅቶችን ፣ ለተማሪ አገልግሎት ሰአቶች አስቀድመው

የተፈቀደ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ፣ ተማሪዎችና ቤተሰቦች ለማገዝ ሳምንቱን በሞላ ብዙ መንገዶች አሏቸው።

የፕሮጀክቶችን ዝርዝር በሚመለከት ከሴፕቴምበር አጋማሽ ጀምራችሁ የMontgomery County ማእከልን Community Service Week page/የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምነት ገፅ ተመልከቱና ከፍላጎታችሁ ገር የሚሄዱ የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም ምረጡ። ት/ቤቶችና PTAዎች የአገልግሎቱ ሳምንት አካል በማድረግ የበጎ-ፈቃድ ፕሮጀክቶች ፕላን እያደረጉ ነው። የት/ቤት ማህበረሰባችሁ ምን እያደረገ ነው?

ለመሳተፍ የሚፋልግ የሰፊ ቡድን አባል ከሆናችሁ፣ ወይም ፕሮጀክት ማስተናገድ የሚፈልግ ከአንድ ትርፍ-የለሽ ድርጅት (ት/ቤት ወይም PTA) ጋር ግንኙነት ካላችሁ ለservicedays@montgomerycountymd.gov ኢሜይል አድርጉ ወይም ለበጎ-ፈቃደኛ ማእከል በ240-777-2600 ደውሉ።

**የMontgomery አለም በአል ባህላዊ አይነተ-ብዙህነትን ያከብራል**

የMontgomery አለም በአል የMontgomery County እና የዋሺንግቶን፣ ድ.ሲ. አካባቢ ሃብታም ባህላዊ ቅርሶችን ያከብራል ትርእይትም ያሳያል። በአሉ የሚካሄደው እሁድ፣ ኦክቶ. 16፣ በMontgomery ኮሌጅ ሮክቪል ካምፐስ፣ 51 Mannakee Street in Rockville፣ ከቀትር እስከ 4 p.m. ነው።

በዚህ አመት በአል MCPS ሽርከኛ/ተባባሪ በመሆኑ ይኮራል። ነፃው ክውነት የሚያካትታቸው አለማቀፍ መንደር፣ አለማቀፍ ወጥ ቤት ከባህላዊ ምግብ ትእይንት በዋና ወጥ ቤት፣ የእጅ ስራ ገበያ፣ የባህሎች ሰልፍ፣ ሁለት የባህላዊ ጭፈራና ሙዚቃ መድረኮች፣ በአገልግሎቶች ግንኙነቶች፣ ባህላዊ ኪነጥበባት፣ እና ጨዋታና የእርስበርስ እንቅስቃሴዎች ለሞላ ቤተሰብ። ለተጨማሪ መረጃ www.worldofmontgomery.comን ጎብኙ።

**የMontgomery County የህዝባዊ ቤተመፃህፍት ሽርክና ለወጣቶች ቪድዮ አመራረትና ግራፊካዊ ቀረፃ ትምህርት ያቀርብላቸዋል**

የMontgomery County ህዝባዊ ቤተመፃህፍቶች ከGandhi Brigade/ጋንዲ ብርጌድ ጋር በመሻረክ ነፃ የቪድዮ አመራረትና ግራፊክ ቀረፃ ትምህርቶች ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች ይሰጣል።

የሽርክና ፕሮግራሙ ለተማሪዎች በFinal Cut Pro ቪድዮ ማዘጋጃ ሶፍትዌር በመጠቀም የቪድዮ አመራረት እና በPhotoshop፣ Illustrator እና InDesign በመጠቀም የግራፊክ ቀረፃ መሰረቶች ለመማር ለተማሪዎች እድል ይሰጣል።

የ12-ሳምንት ትምህርቶች በአምስት ቤተመፃህፍት ይሰጣሉ። ፕሮግራሙ ከ3 እስከ 5 p.m ይሰበሰባል እና በሴፕተምበር 19 ሳምንት ይጀምራል።

**የሚከተሉት ቅርንጫፎች ሰኞ ፕሮግራሞች ያቀርባሉ፡-**

- Rockville Memorial Library, 21 Maryland Avenue
- Silver Spring Library, 900 Wayne Avenue
- White Oak Library, 11701 New Hampshire Avenue

**የሚከተሉት ቅርንጫፎች ማክሰኞ ፕሮግራሞች ያቀርባሉ፡-**

- Olney Library, 3500 Olney-Laytonsville Road
- Gaithersburg Library, 18330 Montgomery Village Avenue

**ምዝገባው በ**https://goo.gl/is4y58 **ይገኛል**

**ለተጨማሪ መረጃ፣** Mary Ellen Icaza/**መሪ ኤለን ኢካዛን በ**240-777-0006 **ደውሉላት።**

MCPS **በዜናዎች**
**ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎትን? ስለ**MCPS **ወቅታዊ ርእሰአንቀፆች፣ ቪድዮዎች፣ እና ጋዜጣዊ መግለጫዎች ጥቂቶቹንም ቢሆን ማየታችሁን አረጋግጡ።**

***ቪድዮዎች***

የኦሊምፒክ የወርቅ ኒሻን ተሸላሚ Cashell ESን ጎበኘ/ች

***የMCPS ት/ቤቶች በዜናዎች***
**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አዲስ የማክበር መንገድ፣ የፈተና ውጤቶች ሳይታዩ**
Northwest High School **ብሄራዊ 'የእድል ት/ቤቶች' የብር እውቅና ተቀበለ**

***ጋዜጣዊ መግለጫዎች***
Northwest High School **ብሄራዊ 'የእድል ት/ቤቶች' የብር እውቅና ተቀበለ**
**የትምህርት ቦርድ ስለ ት/ቤቶች መከፈት ማስታወሻ/ዘገባ ተቀበለ፤ የምደባዎች ተጠያቂነት ላይ ተወያየ**